# ቶኒ ብሌርና መንትዮሽ ስብዕናው

"እንደኔ እንደኔ ከሁሉም በላይ የቁርዓን አስደናቂነቱ የተራማጅነት ይዘቱ ነው፡ የሌላ ዕምነት ተከታይ እንደመሆኔ ይህን ፅሁፍ በታላቅ ትህትና ፅፈዋለሁ፡፡ ከዕምነቱ ውጭ እንዳለ ሰው ሳየው ቁርዓን የተሃድሶ መፅሃፍነቱ ግርምት ይፈጥርብኛል፡፡ ክርስትናና ያይሁድ ዕምነት ወደመሰረታቸው ይመለሱ ዘንድ ጥሯል ልክ ቤተክርስቲያን ከክፍለዘመናት በኋላ ተሃድሶን ሊያመጡላት እንደሞከሩት የለውጥ ሰዎች ሁሉ፡፡ ቁርዓን ሁሉን አቀፍ ነው፣ ሳይንስና ዕውቀትን ሲያደንቅ እንደጥንቆላ ያለውን ባዕድ አምልኮ የሚጠላ፣ ተግባር ላይ ለማዋል የሚያመች፣ ስለ ሴቶች፣ ስለትዳር፣ ስለ አስተዳደር ያለው አመለካከትም ከጊዜው በዕጅጉ የቀደመ ነው፡፡

በርሱ አመራር *(ቁርዓኑን ማለታቸው ነው)* የዕስልምና መስፋፋትና ቀድሞ ክርስቶስ አሊያም ጣዖታት በሚመለኩባቸው ግዛቶች ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ አጀብ የሚያስብል ነው፡፡ እስልምና ለክፍለዘመናት መዝለቅ የተቻለው ስርወመንግስት በመመስረት አለምን በፈጠራ፣ በጥበብ፣ በባህል መምራት ሲችል በመካከለኛው ዘመን መጀመሪያም የመቻቻል ተምሳሌት የሆኑ ቦታዎች ከክርስቲያን ግዛቶች ይልቅ በሙስሊም ግዛቶች የመገኘታቸው ዕድል የሰፋ ነበር"

አንግዲህ ይህ ከላይ ስለእስላም እና ቅዱስ መፅሃፉ ቁርዓን የተጠቀሰው ሁሉ "ኤ ባትል ፎር ግሎበል ቫልዩዝ" በተሰኘና እንዳውሮፓዊያኑ አቆጣጠር በ2007 ለንባብ ከበቃ አንድ ፅሁፍ የተወሰደ ነበር፡፡

ይህ አቋም ዓለም ባስተዋይነታቸው፣ ባመዛዛኝነታቸውና ለሰው ደግን በመመኘት የላቀ ስርፋ በሰጣቸው እንደ ኔልሰን ማንዴላ፣ ማሃትማ ጋንዲ ወይም ሌሎች ብልህ ሰዎች ተንፀባርቆ በነበር ደግ፡ ግና ይህ ከቶኒ ብሌር መንትያ ስብዕናዎች ያንዱ መገለጫ መሆኑ ነው የመገረሜ መነሻ፡፡

ይህን መሰሉን አቋም ከግለሰቡ እውነተኛ ማንነት፣ በቅርብ ጊዜው የዓለማችን ፖለቲካ ውስጥ ስለተጫወቱትና በመጫወት ላይ ስላሉት አጠቃላይ ሚና ለማየት መሞከርን ወድጃለሁ፡፡ እኚህ ሰው ግለ ታሪካቸው እንደሚያስረዳው በ1994 የሌበር መሪ የሆኑበትና የኋላ ኋላም በ1997 ወደጠቅላይ ሚኒስተርነት የተምዘገዘጉበት ሂደት ብዙዎችን ያስገረመ ሲሆን ለኋለኛው ማንነታቸውም መሰረት የጣለ ነበር ማለት ይቻላል፡፡

የሁለተኛውን የአለም ጦርነት ተከትሎ በተፈጠረው አዲስ የአለም የኃይል አሰላልፍ ውስጥ ብሪጣንያን በበላይ ሹምነት ከመሩት የክሌመንት ኧትሊ፣ ሃሮልድ ዊልሰንና ጀምዝ ካላሃን መንግስታት በቀር ብዙም ነገሬ

ያልተባለለት ሌበር ፓርቲን ካቀረቀረበት ቀና ያደረጉ፣ እርሱ እንጂ ወግ አጥባቂዎቹም ሆኑ ሊበራል ዲሞክራቶቹ አንዳች ይፈይዱት የሌለ እስኪመስል ድረስ ከፖለቲካው ሸራ ቀለማቸው ጎልቶ እንዳይታይ እንዲደበዝዝ ያደረጉ፣ ለተናገሩት ሁሉ ድጋፍ፣ ሙገሳ የተቸራቸው፣ ቀድመዋቸው የስልጣን ዕርካብን በረገጡት ማርገሬት ታቸርና ጆን ሜጀር ዘመን ሌበር አጥልቶበት ከነበረው የወግ አጥባቂዎች ክፉ ጥላ የገላገሉት፣ የገጠመውን ድክመት መቀልበስ የቻሉ፣ ለፓርቲውም ሆነ ለሃገሬው ሰው ድንቅ መሪ ነበሩ-እኚሁ ብሌር፡፡

ከፓርቲያቸው ጀምሮ ጤናን፣ ትምህርትን፣ የመንግስት ሰራተኞች አስተዳደርን በምድረ ብሪጣንያ አዲስ መልክ ሲያሲዙና የሰሜን አየርላንድ ችግር ሰላማዊ መፍትሄ ያገኝ ዘንድ አብይ ሚና ሲጫወቱ፣ ከዚያም አልፎ ግጭት የሚያብጣቸውን አካባቢዎች ለማረጋጋት በሚል በቀድሞዋ ዩጎዝላቪያ፣ በአፍሪካይቱም ሃገር ሲየራሊዮን ሃገራቸው ወታደራዊ ተሳትፎ እንዲኖራት አድርገዋል፡ ተሳትፏቸው ካስከተለው ውጤት አንፃር ለአንዳንዶች ግሩም ማድረጋቸው፣ ጀግንነታቸው ሲጎላ ባንፃሩ ወታደራዊ ዕርምጃዎቻቸውን፣ አላማቸውን በእኩይ የፈረጁባቸው መኖራቸውን ለማየት የሰርብና የአናሳ አልቤኒያውያኑን አቋም መፈተሽ ይበቃ ይመስለኛል፡፡

በኮሶቮ አዳዲስ ህፃናትን ቶኒብሌር እያሉ እስከመሰየም የተደረሰላቸው ፖለቲከኛ ነገር አለሙ ሁሉ እንዳሰቡት አሊያ እንደተመኙት የሄደላቸው ስላለመሆኑ ፍንጭ መታየት የጀመረው ግን ያለንባትን አለም ሁለንተናዊ ሁኔታ የቀየረ፣ ወደ ሌላ ምዕራፍ ያሻገረ የተባለለትና ሺዎች ንፁሃን የረገፉበት፣ ከዘጠኝ አመታትም በኋላ ያወዛጋቢነቱ ትኩሳት ያልበረደው የመስከረም አንዱ ጥቃት መፈፀምን ተከትሎ እንደሆነ ማጤን ይቻላል፡፡

ዛሬ ዛሬ ከዩኤስ አሜሪካ ወገን የሚደርስባቸው ፈርጀብዙ ጫና ያበሳጫቸው የኢራኑ መሪ አህመዲነጃድ በተደጋጋሚ የይጣራ ጥያቄ የሚያነሱበት ይኸው የመስከረም አንዱ ጥቃት ገና እንደተፈፀመ “በአንዳችን ላይ የተፈፀመ ጥቃት በሁላችንም ላይ እንደተፈፀመ ያህል ነው” ላለው የሰሜን አትላንቲክ ሃገራት ቃልኪዳን ድርጅት (ኔቶ) ይሁንታቸውን ሲሰጡ፣ እንደምንጊዜውም ሁሉ የቀድሞዋ ሎሌያቸው አሜሪካ ለያዘችው አቋም እንደጌትነቱም ባይሆን እንደተከበረች ወዳጅነቷ ሃገራቸውን ከሁሉ ቀድመው ከአሜሪካ ጎን አሰልፈዋል፡፡

የቀድሞዋ ሶቪየት ህብረትን ከአፍጋኒስታን ጠራርጎ በማስወጣቱ ረገድ አክብሮት የተቸራቸው ኋላ ግን በምስራቅ አፍሪካ ዳሬሰላምና ናይሮቢ የአሜሪካ ኤምበሲ ጥቃቶች ላይ በአቀነባባሪነት የተፈረጁትና ይሄንኑም የ9/11 (መስከረም አንድ መሆኑ ነው) ጥቃት ፈፀሙ ለተባሉት ፣ ታላፊነቱንም እወስዳለሁ

ላሉት ሰው አሳማ ቢን ላደንና ለጋሻጃግሬዎቻቸው መጠለያና የልምምድ ቦታ ፈቅዷል ተብሎ የተወነጀለውን፣ ከፓኪስታንና ሰዑድ አረቢያ በቀር የሚያውቅ የሚያቀርበው ያልነበረውን የአፍጋኒስታን ኢስላማዊ መንግስት- ታሊባንን ከመንበሩ በማስወገድ አንፃርም የቀሰቀሷቸው ጦርነቶች ሁሉ ቅዱስ እንደሆኑ የሚሰማቸው ቡሽ "በአለም አቀፍ ሽብርተኝነት ላይ ዘመቻ ከፈትኩ" ሲሉ ብሪጣንያ ጉልህ ሚና እንድትጫወት አስችለው ነበር- ብሌር፡፡ ይህ አጀማመሩ እንጂ አፈፃፀሙ ዋዛ ያልሆነው፣ የመውጫ ስልት ቀድሞ በወጉ ያልተበጀለት የአፍጋኒስታን ጦርነት አሜሪካ መራሹን ጦር ከአረንቋው ከዶለ እነሆ ዘጠኝ አመታት አለፉ፡፡

በስልጣን ዘመናቸው ያስተናገዷቸው ክስተቶችና ለነርሱ የሰጡትም ምላሽ እጅግ ተጠይ ያደረጋቸውን ጆርጅ ዳብሊው ቡሽን በማገዝ: አለም ይቆይ በደምብ ይጤን ያለውን ግና እርሳቸው አስቸኳይ ያሉትና ሳዳምን ከስልጣን የማስወገድ (ሬጊም ቼንጅ)፣ እና ኢራቅ ያሏትን ጅምላ አውዳሚ መሳሪያዎች (እንደሌሏት ስዊድናዊው የአለምዓቀፉ አቶም ተቆጣጣሪ ድርጅት አይ ኤ ኢ ኤ መሪ ሃንስ ብሊክስ አረጋግጠዋል) የማስፈታት ተልዕኮ መጀመራቸው፣ ወደዚህ ውሳኔ አደረሰን ሲሉ የተጠቀሙበት ምክንያትም የብሌርን ፍፃሜ አስቀያሚ ካደረጉት ሁሉ ግንባር ቀደሞቹ ናቸው፡፡

በኢራቅ ጅምላ ጨራሽ መሳሪያ አንፃር አለኝ ያሉትና የመንግስታቸውን ሃሳብ ያንፀባረቀ የተባለለትን ዶሴ ሲያቀርቡ በአርባ አምስት ደቂቃ የለኩትን የሳዳም መሳሪያዎች ስጋት መሻጣቸው ለባለጉዳዮቹ ሳቢ ይሆን ዘንድ ሆን ብለው ያጋነኑት እንጂ እውነታን የማያንፀባርቅ መሆኑ ይፋ ከመደረጉ ጋር ተያይዞ ብሪጣንያ ሁነኛ የአውዳሚ መሳሪያዎች ጠቢቧን ዶ/ር ዴቪድ ኬሊን ማጣቷም የቶኒ ብሌርን መከራ አብዝቶት አንደሁ እንጂ ለዝናቸው መላቅ አልበጀም፡፡

አምባገነን ያሏቸው ሳዳም ሁሴንን ከስልጣን በማስወገድ ነፃነትን፣ ዲሞክራሲን፣ ፍትህ፣ ዕኩልነትን ከኢራቅ አልፎ በመካከለኛው ምስራቅ እናዳርሳለን ሲሉ ቡሽና ባልንጀሮቻቸው የገቡት ቃልም ያችን መከራዋ የበዛ ሃገር ሕዝቦች መግደል መፍጀቱ፣ ለስደት መዳረጉ እንጂ መካከለኛው ምስራቅ የተገባለት ቃል ሰምሮ፣ አሜሪካና ሸሪኮቿም የዲሞክራሲ አከፋፋይነታቸው ነገር ሲያፈራ አልታየም፡ ይልቁንም ነፃ ሊያወጣ የገባ ጦሯ ወንድማማቾችን ደም አቃብቶ፣ ጦሱ ሲብስ ከወራሪውም የምሱን ወስዶ ኃያል ሃገር አሜሪካም የተረፈ ኃይሏን ከነሽንፈቱ ታስወጣ ዘንድ ግድ አላት እንጂ፡፡

ምንም እንኳ ስለ እስልምናና ቅዱስ ቁርዓን ባደባባይ ያሉትን ቢሉም ሙስሊም በዛሽ በሆኑ ያካባቢው ሃገራት አንፃር ያደረጉ ያስደረጉት፣ ዛሬም የእስራኤል ፍልስጤምን ጉዳይ ለሚከታተለውና አሜሪካ፣ ራሺያ፣ የአውሮፓው ህብረትና የተባበሩት መንግስታትን ባንድ ላቀፈው ያራትዮሽ ድርጅት እየሰሩ ያለውን

ለተመለከተ ቶኒ ብሌር በርግጥ እንዳሉት ያን ከጊዜው የቀደመ መፅሃፍ (ቁርዓን) መመሪያችን ያሉ ሰዎች (ሙስሊሞች) እርሳቸው ሰርከ እንደሚሰብኩት ያለ መልካም እሴት እንደሚኖራቸው ያምናሉ ለማለት አያስደፍርም፡፡ ህልቆ መሳፍርት የሌላቸው ኢራቃዊያንን የጨፈጨፉ ያስጨፈጨፉት፣ ቤተሰቦቻቸው ላይ በተፈፀመ የመርዛማ መሳሪያ ጥቃት ከተለመደው አፈጣጠር በተለየ ለተወለዱና የአካል ጉዳት ለደረሰባቸው ሕፃናት ሰቆቃ ሁሉ ከተጠያቂዎቹ የሆኑት ሰው ብሌር፣ እንደሁሌውም “ሙስሊም አክራሪነት” ሲሉ የሚጎስሙትን ነጋሪት ለሚያደምጥ፣ ሰውዬው ያስመስሉ እንደሁ እንጂ በፍልስጤምም ሆነ በሩቅ ላሉ ሙስሊሞች በጎን ያደርጋሉ ማለት ሲበዛ ነው የሚያጠራጥረው፡፡

መካከለኛው ምስራቅን በጥብጠው ሳለ እዚያው የሰላም አፈላላጊ ተደርገው መሰየማቸው በርግጥ አስቂኝና አስገራሚ ቢሆንም በምዕራባዊያን ተፅዕኖ ስር ለአስርት አመታት ለቆየው ያካባቢው ሕዝብ አማራጭ አልነበረውምና ብሪጣንያ አነሳሱ ቢያምርም አጨራረሱ አስቀያሚ የሆነ ፖለቲከኛዋን ገለል ታደርግበት ቦታ አላጣችም ነበር፡፡

ቶኒ ብሌር ለፖለቲካዊ ውድቀታቸው ምክንያት ተደርገው ከሚታሰቡት አንዱ የሆነው የኢራቅ ጦርነት በተቀሰቀሰ ጊዜ በርካቶቹን አውሮፓዊ ሃገራት ችላ ብለዋቸው፣ ተራማጅ እንዳልሆኑ በቆጠሯቸው ማግስት የዘመቱበት ምክንያት ሃሰትነቱ ታውቆ፣ ከአትላንቲክ ባሻገር የመሰረቱት የዘመቻ ወዳጅነት አውሮፓዊያኑ እንዳስጠነቀቁት ባልተጣራ ስጋት ላይ የተመሰረተ መሆኑን አለም ለመታዘብ ችሏል፡፡ ቅሌቱ ያስከተለው ፖለቲካዊ ክስረት ሳይረብሻቸው ከፍተኛ የዲሞክራሲያዊ ስርዓት ባልቤት የሆኑ ሃገራትን ላቀፈው የአውሮፓ ህብረት በፕሬዚደንትነት ለማገልገል ብራሰልስን ቋምጠው እንደነበር ስንመለከት የሰውዬውን የሁሌዜም የማይረካ የስልጣን ጥም እንረዳለን፡፡

ዛሬም ድረስ ውስጣዊ ፀፀት ካልፈጠረባቸውና በየሙስሊም ግዛቶቹ ካፈሰሱት ደም አንፃር ሲለካ ያ ምኞታቸው ሰምሮ በቤልጀማዊው ኸርማን ቫን ሮምፖይ የተያዘውን የ አውሮፓ ህብረት ፕሬዝደንትነት መንበር ተቆናጠውት ቢሆን ኑሮ በሙስሊሞች ላይ ይደቅኑ የነበረውን ፈተና መገመት አይከብድም፡፡ አለመመረጣቸው በርግጥም ሁሉን አቀፍነቱን የመሰከሩለት፣ ሳይንስና ዕውቀትን ሲያደንቅ ባዕድ አምልኮን ይዋጋል ያሉት፣ ተግባር ላይ ለማዋል የሚያመች፣ ስለ ሴቶች፣ ስለትዳር፣ ስለ አስተዳደር ያለው አመለካከትም ከጊዜው በዕጅጉ የቀደመ ስለመሆኑ የመሰከሩለት ቁርዓን ለሚመራቸው አማኞች (ሙስሊሞች) ታላቅ እፎይታነቱን መገመት ይቻላል- ሰላም፡፡